# አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
# UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)

---

ቀን ____________

**ለክብር አቶ ግርማ ወልደጊዮርጊስ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ፕሬዝዳንት**

**ለክብር አቶ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ሪት ብርትኳን ሚደቅሳ ከሐምሌ 13 ቀን 1999 ዓ/ም ከእስር የተፈቱት በክብር ፕሬዝዳንቱ በተሰጣቸው ይቅርታ መሆኑ ይታወቃል። መንግስት ይቅርታውን የሰጠው 18 ወራት በፈጀ የአገር ሽማግሌዎች ጥረት በመሆኑ የአገር ሽማግሌዎቹ በዚህን ዕለት ባወጡት መግለጫ ተገልጿል። መንግስት ለሰጠን ቀና ምላሽ እና ለተከሳሾች ለተደረገው ምህረት ከፍተኛ ምስጋናችንን እናቀርባለን እስረኞችም የቀረበውን ሃሳብ ተቀብለው ለጥረታቸው ለሰጠው በጎ ምላሽ እና ላሳዩት ትብብር በፈጣሪ ስም እናመሰግናለን ብለዋል። ይህን አነጋገር የይቅርታው ሂደት የተከናወነው በሽማግሌዎቹ አማካኝነት መሆኑ በማያወላውል መልኩ ያረጋግጣል። ለወ/ሪት ብርትኳን የተሰጠው ይቅርታ ጥያቄ ሲነሳ የቻለው ወ/ሪት ብርትኳን አውሮፓ በሄዱበት ወቅት በሰጡት መግለጫ የአገሪቱ ህግ በሚያዘው መሰረት ደብዳቤ ጽፌ የጠየኩት ይቅርታ የለም ብለዋል ተብለው ነበር ወ/ሪት ብርትኳን አውሮፓ ሄደው ባደረጉት ንግግር ይቅርታ መጠየቃቸውን እንደካዱ ተቆጥሮ ማስተባበያ እንዲሰጥበት መንግስት ይጠይቃል። ፓርቲውም ወ/ሪት ብርቱኳን በአውሮፓ በሰጡት መግለጫ መሳሳታቸውን በመገንዘብ ወ/ሪት ብርቱኳን ማስተካከያ መግለጫ እንዲሰጡበት ይወስናል። ወ/ሪት ብርትኳንም በቀረበላቸው ጥያቄ መንግስትም ህዝብም እንዲያውቅ ቃሌ ይሄው ነው በሚል ጋዜጣዊ መግለጫ በሽማግሌዎቹ አማካኝነት ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ሰነድ መንግስት እና ህዝብም ይቅርታ ጠይቄአለው ይህን ቃል ለለውጠውም ሆነ ልክደው በምንም አልችልም በማለት በማያሻማ ሁኔታ ገልፀዋል። ይቅርታ መጠየቃቸውንና መፈረማቸውን እንዳመኑ ታህሳስ 20 ቀን 2001

ዓ.ም ይቅርታው ተገልብጦ የእድሜ ልክ እስራት ተፈፃሚ እንዲሆን ወደ ማረሚያ ቤት ተላኩ የፍትህ ሚኒስቴር የውሳኔውን መሰረዝ ባወጣው የመመሪያ መግለጫ የተጠቀሰው የአዋጅ ቁጥር 395/96 አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 እንደሆነ ገልጿል። ፍትህ ሚኒስቴር ለይቅርታው መነሳት የተጠቀመባቸው የአዋጅ አንቀፆች ሲታዩ የወ/ሪት ብርትኳን ይቅርታን ለማንሳት በምንም ሁኔታ አግባብነት የሌላቸው ሆነው ተገኙ ምክንያቱም ወ/ሪት ብርትኳን ይቅርታ ያገኙት በማስመሰል ወይም ለማታለል ብለው የሚያሰኝ ማስረጃም ሆነ የተፈፀመ ተግባር አልነበረም። የይቅርታ መጠየቂያው ደብዳቤ የተዘጋጀው እና ወደ ሚመለከተው አካል የደረሰው ረዥም ጊዜ ጥረት ባደረጉት አገር ሽማግሌዎች እንደመሆኑ መጠን የማጭበርበር ወይም የማታለል ተግባር አለመኖሩ አስታራቂዎቹ በሽማግሌዎች እርቅ ማድረጊያ መንገድ ነው በማለት መናገራቸው የሂደቱን ሃቅ ወይም ደግሞ Statement of fact ከማረጋገጥ ሌላ የትኛው ሁኔታ አይደለም የፍትህ ሚንስቴር መጀመሪያ በሰጠው መግለጫ ላይ የጠቀሰው አንቀጽ ጉልህ ስህተት መሆኑን 48 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ከመጀመሪያው መግለጫ ሌላ መግለጫ አወጣ ፍትህ ሚኒስቴር ለሁለተኛ ጊዜ ባወጣው መግለጫ አዋጅ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 ተገለፀ በዚህም ቢሆን የተፈፀመ ተግባር እንደሌለ ግልጽ ነው። ይቅርታው የተሰረዘው ከዚህ በፊትም ከሃቅ ውጪ ነው የሚልባቸው ዋና ዋና ነጥቦቹ፡-

- ወ/ሪት ብርትኳን ይቅርታ የጠየቀች መሆኑ በግልጽ ማረጋገጧን
- ፍትህ ሚኒስቴር በመጀመሪያ መግለጫው ይቅርታውን ለመሰረዝ ተጠቅሜበታለሁ ያለውን የአዋጁን አንቀጽ የለወጠ መሆኑ ሲታይ ይቅርታው ለማሰረዝ ውሳኔ ላይ የተደረሰው ከመሰረቱ የህግ ድጋፍ ሳይኖረው መሆኑ ስለሚያረጋግጥ፣
- ፍትህ ሚኒስቴር ለሁለተኛ ጊዜ ለማስተካከያነት የተጠቀመባቸው አዋጆች እና አንቀፆች በተግባር ላይ ሆኖ አለመገኘታቸው፣
- ወ/ሪት ብርትኳን ይቅርታ ጠይቄአለሁ ይቅርታ መጠየቄን አልካድኩም ልክድም አልችልም በማለት በጋዜጣ መግለጫቸው ቢያረጋግጡም ህዝብን ለማሳመን ክደዋል እየተባለ በሬዲዮ በቴሌቪዥን እና በመንግስት ጋዜጣ ላይ መገለፁ፣

- ለወሪ/ት ብርትካን የተሰጠው ይቅርታ ከተነሳና እሳቸው ከታሰሩ በኋላ ህዝብ አስተያየት እንዲሰጥበት በየመስሪያ ቤቱ በየቀበሌ ነዋሪ የስብሰባ መወያያ መሆኑ ግን የሚያሳስብ በጥፋታቸው ሁኔታ ሲታይ የተፈጠረውን የህግ ስህተት ለመሸፈን የሌለውን ጥፋት በህዝብ አእምሮ ውስጥ እንዲፈጠር ለማድረግ ከመሆኑም በላይ የሽምግልናውን የረዥም ጊዜ ውጤት ዋጋ ቢስ የሚያደርግ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ይህ ህግ እና ስነ-ስርዓት የሚፈፀመው ወሪ/ት ብርትኳን ያቀረቡትን የይቅርታ ጥያቄ እና የሽማግሌዎቹን የረጅም ጊዜ ጥረት ዋጋ ቢስ ሆኖ እንዲገኝ መደረጉ የሚያሳዝን ሲሆን ለወ/ሪት ብርትኳን የተሰጠው የይቅርታ ውሳኔ ተግባራዊ እንዲሆን በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን።

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
(አንድነት)
ማዕከላዊ
ጽ/ቤት
UNITY FOR DEMOCRACY AND ... PARTY (UDJ)